

በሐሙስ ፡ ቀን የሚነበብ፡ የቅዱስ ፡ ያሬድ ፡ ገድል።

፩ ፡ አንድ ፡ አምላክ ፡ በሚሆን ፡ በአብና ፡ በወልድ ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስ ፡ ስም ፡ በዕለተ ፡ ሐሙስ ፡ የሚነበብ ፡ የቅዱስ ፡ ያሬድ ፡ ካህን ፡ ገድልና ፡ ምሥክርነት ፡ የቅዱስ ፡ ያሬድ ፡ ጸሎትና ፡ በረከት ፡ ከአገልጋዮቹ ፡ ከ

ና ፡ ከ ጋር ፡ ይኑር ፡ ለዘለዓለሙ ፡ አሜን።

፪ ፡ መጽሐፍዋም ፡ ውስጧና ፡ ላይዋ ፡ በየሰባት ፡ ማኅተም ፡ የታተመችና ፡ ረአዬ ፡ ኅቡአት ፡ ወልደ ነጐድጓድ ፡ ዮሐንስ ፡ በዘመነ ፡ ክርስቶስ ፡ የሚል ፡ የተጻፈባት ፡ ናት ፡ ከተሰቀለና ፡ ከተነሣ ፡ በኋላ ፡ ማኅተምዋን ፡ ሊፈታ ፡ የሚገባው ፡ ወንጌላዊ ፡ ዮሐንስ ፡ እንዳለው ፡ ነው ፡ ያለቀሱም ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ፡ ያች ፡ መጽሐፍ ፡ ያያት ፡ይገልጣት ፡ ዘንድ ፡ የሚገባው ፡ አልተገኘምና ፡ ከነዚያ ፡ አለቆች ፡ አንዱም ፡ አታልቅስ ፡ አለኝ ፡ ያች ፡ መጽሐፍን ፡ ይገልጣት ፡ ማኅተሟንም ፡ ይፈታ ፡ ዘንድ ፡ ከዳዊት ፡ ትውልድና ፡ ከይሁዳ ፡ ነገድ ፡ እነሆ ፡ አንበሳ ፡ ወጣ።

፫ ፡ ጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስም ፡ ዮሐንስ ፡ ወልደ ፡ ነጐድጓድን ፡ ያየኸው ፡ የነበረ ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ያለውን ፡ ጸሐፍ ፡ አለው ፡ የሚለውም ፡ ድንግል ፡ ጎሊና ፡ ድንግል ፡ ሥጋ ፡ ከሆነች ፡ ማርያም ፡ ከተወለደ ፡ ጀምሮ ፡ እስኪሰቀል ፡ በዓለም ፡ የነበረው ፡ ነው ፡ ሰላሳ ፡ ሦስት ፡ ያኽል ፡ የታተመች ፡ መጽሐፍም ፡ ያዛት ፡ ማኅተምዋንም ፡ ፈታ ፡ የሚለውም ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ እስከ ፡ ዓለም ፡ ፍጻሜ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ያለው ፡ ነው።

፪ ፡ ረአዩ ፡ ኅቡአት ፡ ዮሐንስ ፡ የሚለውን ፡ አንዱ ፡ ና ፡ እዩ ፡ አለኝ ፡ ቃልንም ፡ እንደ ፡ ነገሮድጓድ ፡ ሰማሁ ፡ ነጭ ፡ ፈረስንም ፡ ሲመጣ ፡ አየሁ ፡ የሚጫነውም ፡ ጦርን ፡ ያጠናል ፡ አክሊልንም ፡ ሰጡት ፡ እንዲሸነፍም ፡ ወጣ ፡ ለነጭ ፡ ፈረሱ ፡ የተጫነውም ፡ ዓለምን ፡ ያዳነ ፡ ክርስቶስ ፡ ነው።

፫ ፡ ዳግመኛም ፡ ታኦሳሎስ ፡ የተባለ ፡ ዮሐንስ ፡ ስለበጉ ፡ ሙርግ ፡ አለ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ወደሆነ ፡ ይህ ፡ የእውነት ፡ ቃል ፡ የተጠሩ ፡ ብፁዓን ፡ ናቸው ፡ ብለህ ፡ ጻፍ ፡ አለኝ ፡ ዳግመኛም ፡ አለ ፡ ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ሰማይ ፡ ተከፈተ ፡ ነጭ ፡ ፈረስም ፡ ወጣ ፡ የሚጫነውም ፡ ስሙ ፡ በእውነት የሚፈርድ ጻድቅና እውነተኛ ነው ክርስቶስ በነጭ ፈረስ ፡ የመጽሐፍ ፡ ማኅተምን ፡ ይፈታ ፡ ዘንድ ፡ እንደመጣ ፡ እንዲሁ ፡ ዳግመኛ ፡ በነጭ ፡ ፈረስ ፡ የሚመጣ ፡ ረአዩ ፡ ኅቡአት ፡ ዮሐንስ ፡ ወልደ ፡ ነጐድጓድ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ነው ፡ የነጭ ፡ ፈረስ ፡ ትርጓሜውም ፡ ኅቡእ ፡ ነው ፡ በነጭ ፡ ፈረስ ፡ የተጫነውም ፡ ጦርንም ፡ የሚጠነክር ፡ አክሊልንም ፡ የሰጡት ፡ አዳም ፡ ነው የሚለው ፡ ያሸነፈው ፡ አይደለም ፡ አዳም ፡ እንደተሸነፈ ፡ እሱ ፡ ግን ፡ ተሸነፈ ፡ ነቢዩ ፡ ዕዝራ ፡ ፈተኛው ፡ አዳም ፡ ክፋትን ፡ ለብሶ ፡ ተሸንፏልና ፡ አለ።

፮ ፡ እሱ ፡ ብቻም ፡ አይደለ ፡ ከሱ ፡ የተወለዱ ፡ ሁላቸው ፡ እንጂ ፡ የታላቁመች ፡ መጽሐፍን ፡ አዳም ፡ ፊታትን? ዮሐንስ ፡ ወልደ ዘብዴዎስማ ፡ መቼ ፡ አለቀሰ ፡ ከነዚያ ፡ አለቆች ፡ አንዱስ ፡ አታልቅስ ፡ መቸ ፡ አለው ፡ ከዳዊት ፡ ትውልድ ፡ የሆነ ፡ ይሁዳ ፡ ከይሁዳ ፡ ነገድ ፡ የተገኘ ፡ አንበሳ ፡ ያች ፡ መጽሐፍን ፡ ይገልጣት ፡ ማኅተምዋንም ፡ ይፈታት ፡ መጣ።

፯ ፡ የከበረ ፡ ያሬድ ፡ ካህንም ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ድምጽ ፡ ይጮሃል ፡ በአምላካችን ፡ ክርስቶስ ፡ ዘመን ፡ ከሃያ ፡ አራት ፡ ካህናተ ፡ ሰማይ ፡ ከሊቃናት ፡ ከነዚያ ፡ አራት ፡ እንስሳም ፡ ወንጌላዊ ፡ ዮሐንስ ፡ ዝማሬያት ፡ እንደሰማ ፡ ሁላቸውም ፡ ዕጣን ፡ የተሞላ ፡ ጽዋን ፡ ያጠናሉ ፡ ያማረ ፡ የበገና ፡ መዝሙርም ፡ የነዚያ ፡ ቅዱሳን ፡ ጸሎታቸው ፡ ነው ያሬድም ፡ አዲሶች ፡ ምስጋናዎች ፡ በክርስቶስ ፡ ትንሣኤ ፡ ዘመን ፡ ያመሰግናል፡ እነሆ ፡ አንበሳ ፡ ከይሁዳ ፡ ነገድ ፡ከዳዊት ፡ ትውልድም ፡ ወጣ ፡ (ተገኘ) ፡ ሲል ፡ አንበሳ ፡ የሚለው ፡ ወልደ ፡ አምላክ ፡ ተነሣ።

፰ ፡ ይህን ፡ ማኅሌትንም ፡ ሠራ ፡ የሚመስለውም ፡ እነሆ ፡ ሁላቸው ፡ ልጆቹ ፡ በቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ውስጥ ፡ በሱራፌል ፡ ምስጋና ፡ ያመሰግናሉ ፡ ከነዚያ ፡ ሰምቶ ፡ እሱ ፡ እንዳስተማራቸው ፡ ስለዚህ ፡ የካህን ፡ ያሬድ ፡ ማኅሌት ፡ ከምድር ፡ እንዳልሆነ ፡ እናውቃለን ፡ ከሱራፌል ፡ ዘንድ ፡ከሰማያት ፡ ናት ፡ እንጂ ፡ ነቢይ ፡ ኢሳይያስ ፡ እንዳለ ፡ በታላቅ ፡ ቃልና ፡ ጩኸት ፡ ማኅሌትን ፡ ተቀበለ።

፱ ፡ ሁለተኛም ፡ ዮሐንስ ፡ ወልደ ፡ ነጐድጓድ ፡ ተናገረ ፡ በነዚያ ፡ ሊቃናት ፡ ፊትና ፡ ከአራት ፡ እንሰሳ ፡ ፊት ፡ ቅዱስ ፡ እግዚአብሔርን ፡ ሲያመሰግኑ ፡ እንደ ፡ ሰማና ፡ እንደአየ ፡ የደብረ ፡ ጽዮን ፡ ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቆመ ፡ አለ ፡ የራሱ ፡ ስምና ፡ የአባቱ ፡ ስም ፡ የቅዱስ ፡ መንፈስ ፡ ስም ፡ ከፈታቸው ፡ የተጻፈባቸው ፡ አሥራ ፡ አራት ፡ እልፍ ፡ ከአራት ፡ ሺሕ ፡ ከእርሱ ፡ ጋር ፡ ነበሩ።

፲ ፡ ቃልም ፡ ከሰማይ ፡ እንደ ፡ ብዙ ፡ ውሀ ፡ ድምጽ ፡ መጣ ፡ እንደ ፡ ነጐድጓድ ፡ ድምጽም ፡ ትልቅ ፡ ነው ፡ በገናዎቻቸው ፡ ሲመቱና ፡ ከመንበሩ ፡ በአዲስ ፡ ምስጋና ፡ በሚያመሰግኑ ፡ ጊዜ ፡ እንደ ፡ በገና ፡ ቃልም ፡ ከነዚያ ፡ ሊቃናትና ፡ ከነዚያ ፡ አራት ፡ እንስሳዎች ፡ ፊትም ፡ ለዚያች ፡ ማኅሌትም ፡ ማወቅዋን ፡ የሚችል ፡ የለም ንጹሐን ፡ ከሆኑና ፡ ከምድረ ፡ ግብጽ ፡ የዳኑ ፡ አስራ ፡ አራትና ፡ አራት ፡ ሺሕ ፡ በስተቀር።

፲፩ ፡ ከሴቶችም ፡ እነዚያ ፡ እንደ ፡ ተወለዱ ፡ ለበግ ፡ ወደሄደው ፡ የተከተሉት ፡ እነዚያ ፡ ናቸው ፡ ከሰው ፡ ልጅ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ለበጉ ፡ ቀድሞ ፡ ማዳን ፡ እነዚያ ፡ አላቸው ፡ ንጹሐን ፡ ናቸውና ፡ ውሸትም ፡ ከአፋቸው ፡ አልተገኘም ፡ ወንጌላዊ ፡ የሚለውም ፡ ፈጽማችሁ ፡ ስሙ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ቅዱሳኖቹ ፡ አዲስ ፡ ምስጋና ፡ ያመሰግናሉ ፡ ይህች ፡ ምስጋናም በፊቼ ፡ ቸትና ፡ በታላቅ ፡ ድምጽ ፡ ነው።

፲፪ ፡ እንዳለውም ፡ ቃል ፡ ከሰማይ ፡ እንደ ፡ ውሀ ፡ ድምጽ ፡ መጣ ፡ እንደ ፡ ብዙ ፡ ውሀና ፡ እንደ ፡ ነጐድጓድ ፡ ድምጽም ፡ አይደለም ፡ ከፍ ፡ ሲል ፡ ነበረ ፡ ዝቅ ፡ ሲልም ፡ ነበረ ፡ ዝቅ ፡ ሲልም ፡ ነበረ ፡ እንደ ፡ ውሀ ፡ ድምጽና ፡ እንደ ፡ ነጐድጓድ ፡ ድምጽ ፡ ጥልቅን ፡ ይመለከታል ፡ በሹክሹክታም ፡ ይሰማል ፡ የሰው ፡ ልብ ፡ ሐሳብም ፡ ያውቃል ፡ የእንዱ ፡ ዕንጨት ፡ ድምጽም ፡ ይሰማል ፡ በመንበሩ ፡ ዙርያም ፡ ትልቅ ፡ ምስጋናውን ፡ ሠራ ፡ የሁሉ ፡ ሥራ ፡ ፍጻሜ ፡ ሲል ፡ እንዲሁ ፡ ያሬድ ፡ ካህንም ፡ ቢታላቅ ፡ ድምጽ ፡ ምስጋናን ፡ ያመሰግናል ፡ የቅዱስ ፡ ያሬድ ፡ ካህንም ፡ በረከት ፡ ከባሮቹ ፡ ከ

ና ፡ ከ ጋር ፡

ይኑር ፡ ለዘለዓለሙ ፡ አሜን።

ተአምር ፡ በል ፡ ሰኞ፡ ላይ ገጽ ፴፩ አለ ።

፩ ፡ ቅዱስና ፡ ምርጥ ፡ ትልቅና ፡ ንዑሕ ፡ የሚሆን ፡ የአባታችን ፡ የማኅሌታዊ ፡ ያሬድ ፡ ዜማው ፡ ጣፋጭ ፡ ተአምር ፡ ምልጃው ፡ ለወዳጁ ፡ ለ
ይጠብቀው ፡ ለዘለዓለሙ ፡ አሜን።

፪ ፡ ያሬድ ፡ ካህን ፡ ገድሉን ፡ ፈጽሞ ፡ ካሣረፈ ፡ በኋላም ፡ ከሱ ፡ መዝሙር ፡ ማኅሌትና ፡ ዋዜማ ፡ አርያምና ፡ ሰላም ፡ ዕዝልና ፡ ዓራራይ ፡ አርባዕትና ፡ ሠለስት ፡ ይሆን ፡ ሁሉ ፡ የሚመስለውም ፡ የብዛቱ ፡ ቁጥር ፡ የምናውቀው ፡ ሠላሳ ፡ እስኪሆን ፡ የተማሩ ፡ የአክሱም ፡ ገበዝ ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ካህናት ፡ ሁላቸው ፡ ጋራ ፡ በጣፋጭ ፡ ምስጋናውም ፡ ሰይጣንን ፡ አሸንፎ ፡ በዚህ ፡ ማኅሌት ፡ እግዚአብሔርን ፡ ሲያመሰግኑት ፡ ኖሩ ፡ ከዘጠኙ ፡ ቅዱሳን ፡ አንዱ ፡ አባ ፡ ሊባኖስ ፡ ደብሩ ፡ አጠገብ ፡ በሰሜን ፡ አቅጣጫ ፡ አክሱም ፡ መቅደስ ፡ ላይ ፡ የመንግሥትነቱ ፡ አዳራሽ ፡ የሆነ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሥ ፡ የካሌብ ፡ ልጅ ፡ የሆነ ፡ ንጉሥ ፡ አፄ ፡ ገብረ ፡ መስቀል ፡ በዘመኑ ፡ እስከ ፡ ድግናይዘን ፡ መንግሥት ፡ ድረስድግናይዘን ፡ ግን ፡ እስራኤላዊ ፡ ነው ፡ ይኩኖ ፡ አምላክም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ በኢትዮጵያ ፡ ነገሠ ፡ ከጫፍ ፡ እስከ ፡ ጫፍም ፡ ዞረ።

፫ ፡ በአንዲት ፡ ቀን ፡ ማዕድን ፡ ሲያደርግ ፡ ካህናት ፡ ወደ ፡ ንጉሥ ፡ ወሰዱትም ፡ በኢትዮጵያ ፡ ጫፍ ፡ አደባባይ ፡ አምና ፡ እንደዛሬ ፡ በተቃጠራችሁ ፡ ጊዜ ፡ ከሚስትህ ፡ ጋራ ፡ እንድትገናኝ ፡ ይሆን ፡ ያህል ፡ ኃይልን ፡ እግዚአብሔር ፡ እነሆ ፡ አደረገልህ ፡ እያሉ ፡ ትንቢትም ፡

ከሰይጣን ፡ በንጉሥ ፡ ላይ ፡ መጣ ፡ ንጉሡም ፡ የእግዚአብሔር ፡ ኃይልን ፡ ዘወትር ፡ ትናገራላችሁ እነሆ ፡ የኔ ኃይልስ ፡ መቼ ትናገራላችሁ ፡ አለ ፡ ስለዚህ ፡ ቃልም ፡ መንግሥትነት ፡ ከሱ ፡ ተቀማ ፡ ምራራ ፡ ለተባለ ፡ ባርያም ፡ ተሰጠ ፡ ምራራም ፡ ከአዳሪ ፡ መውጫ ፡ (ከሽንት ፡ መውጫ) ፡ እንጀቱ ፡ ወጥቶ ፡ ፈጥኖ ፡ ሞተ ፡ ዛጌ ፡ የሚባሉ ፡ አሕዛብም ፡ ነገሡ ፡ እስከ ዜና ፡ ጴጥሮስ ፡ ድረስ ፡ ያ ፡ ዜና ፡ ጴጥሮስም ፡ ሄደ ፡ ከሁላቸው ፡ ሠራዊትና ፡ የደብተራ ፡ ከታቦታቸው ፡ ጋር ፡ ከዳሞት ፡ አውራጃ ፡ ጦርነትን ፡ እንድያደርግ ፡ ሄደ።

፩ ፡በዚያ ፡ ዘመንም ፡ የዳሞት ፡ ገዥ ፡ አረማዊ ፡ መተሎሜ ፡ ነበረ ፡ ጣዖትንም ፡ ያመልክ ፡ ነበረ ፡ ከሱም ፡ ጦርነትን ፡ አደረገ ፡ መተሎሜም ፡ አሸነፈው ፡ ዜና ፡ ማርቆስንም ፡ ራሱን ፡ ቈረጠው ፡ ሠራዊቱ ፡ ሁሉም ፡ የድንኳኑ ፡ ካህናት ፡ ግን ፡ ሮጡ ፡ በታላቅ ፡ ድምጽም ፡ በሃሌ ፡ ሉያ ፡ መዝሙርን ፡ እየተቀኙ ፡ ከታቦታቸው ፡ ፊት ፡ ቆሙ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ታመኑ ፡ በእግዚአብሔርም ፡ ተጠጉ ፡ እርሱ ፡ የምድር ፡ መሠረታት ፡ ሳይፈጠሩ ፡ ከዓለም ፡ በፊት ፡ ንጉሥ ፡ ነውና ፡ የዓለም ፡ መንገድ ፡ ሳይጸናና ፡ የነፋሳት ፡ ኃይሎች ፡ ሳይነፍሱ ፡ ንጉሥ ፡ ነውና።

፫ ፡ የንውፅውፅታ ፡ ድምፅ ፡ ሳይሰማና ፡ የመላእክት ፡ ቁጥራቸው ፡ ሳይቆጠር ፡ ንጉሥ ፡ ነውና ፡ የተክል ፡ ቦታ ፡ ሳይፈጠርና ፡ የአበባዎች ፡ ውበትም ፡ ሳይታይ ፡ ንጉሥ ፡ ነውና ፡ የአርያም ፡ ርዝመት ፡ ሳይታይና ፡ የሰማያት ፡ መሥፈርት ፡ ሳይሰፈር ፡ ንጉሥ ፡ ነውና ፡

የሚመጣ ፡ ዓመት ፡ ኩቴ ፡ ሳይታይ ፡ ሃይማኖትን ፡ ያፀኗት ፡ ሳይሞቱ ፡ ንጉሥ ፡ ነውና።

፮ ፡ የካህናት ፡ አለቆች ፡ ቀንተው ፡ አሳልሰው ፡ ሰጡት ፡ በዕንጨት ፡ ላይ ፡ ሰቀሉት ፡ ስለ ፡ እኛ ፡ ነፍሱን ፡ አሳልፎ ፡ ሰጠ ፡ አምላካችን ፡ ግን ፡ ኃይላችን ፡ ነው ፡ መጠግያችንም ፡ ነው ፡ የብዙ ፡ መድኃኒት ፡ ሥጋውንም ፡ ሰጠን ፡ ከሕያዋን ፡ ጋራ ፡ አንድ ፡ ይሆን ፡ ዘንድ ፡ ከሞትም ፡ ተነሣ ፡ አምላካችን ፡ ግን ፡ ኃይላችን ፡ ነው ፡ መጠግያችንም ፡ ነው ፡ እርሱ ፡ በሰማይ ፡ አለ ፡ ያም ፡ በምድር ፡ አለ ፡ በባሕርና ፡ በጕድጓድ ፡ በቀላይም ፡ አለ ፡ ያም ፡ መድኃኒትን ፡ ለሁሉ ፡ ሰጠ ፡ አምላካችን ፡ ግን ፡ ኃይላችን ፡ ነው ፡ መጠግያችንም ፡ ነው ፡ ያም ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ሰሚ ፡ ጆሮን ፡ ሰጠ ፡ ቀድሞ ፡ ለነቢያት ፡ ዳግመኛም ፡ ለሐዋርያት ፡ በሦስተኛም ፡ ለሊቃውንት ፡ የኡቀት ፡ ጆሮን ፡ ሰጠ ፡ አምላካችን ፡ ግን ፡ ኃይላችን ፡ ነው ፡ መጠግያችንም ፡ ነው።

፯ ፡ ክርስቶስ ፡ የሕይወቴ ፡ መታመኛ ፡ ነው ፡ ምን ፡ ያስደነግጠኛል ፡ አምላካችን ፡ ግን ፡ ኃይላችን ፡ ነው ፡ መጠግያችንም ፡ ነው ፡ ከተመኛ ፡ ብያሸንፈኝ ፡ ልቡናየ ፡ አይፈራም ፡ አምላካችን ፡ ግን ፡ ኃይላችን ፡ ነው ፡ መጠግያችንም ፡ ነው ፡ አሸናፊዎች ፡ ቢከቡኝ ፡ እኔ ፡ ግን ፡ በእርሱ ፡ ታመንኩኝ ፡ አምላካችን ፡ ግን ፡ ኃይላችን ፡ ነው ፡ መጠግያችንም ፡ ነው ፡ አብርሃምን ፡ የረዳ ፡ ያ ፡ ይረዳኛል ኢያሱን ፡ ያዳነ ፡ ያ ፡ ያድነኛል ፡ አምላካችን ፡ ግን ፡ ኃይላችን ፡ ነው ፡ መጠግያችንም ፡ ነው ፡ ሦስት ፡ ልጆች ፡ አናንያና ፡ አዛርያን ፡ ሚሳኤልም ፡ ከሚነድ ፡ እሳት ፡ ያዳነ ፡ በቀንና ፡ በሌሊት ፡ እርሱ ፡ ያድነኛልና ፡

አምላካችን ፡ ግን ፡ ኃይላችን ፡ ነው ፡ መጠግያችንም ፡ ነው ባርያውን ፡ ዳዊት ፡ ከክፉ ፡ ኩናት ፡ ያዳነ ፡ ያ ፡ ያድነኛል ፡ አምላካችን ፡ ግን ፡ ኃይላችን ፡ ነው ፡ መጠግያችንም ፡ ነው ፡ ነፍሴ ፡ ለምን ፡ ታዝኚያለሽ ፡ ስለምንስ ፡ ታውክኛለሽ ፡ እንድገዛለት ፡ በእግዚአብሔር ፡ እመኚ ፡ አምላካችን ፡ ግን ፡ ኃይላችን ፡ ነው ፡ መጠግያችንም ፡ ነው ፡ የአዳም ፡ አምላክ ፡ በጠብ ፡ ጊዜ ፡ ኃይለኛን ፡ ሁኖ ፡ ይቅር ፡ ባይ ፡ ነው ፡ እኔ ፡ ግን ፡ መርዳትንና ፡ ማዳንን ፡ የሚችል ፡ እሱ ፡ አምላክ ፡ ታመንኩኝ።

፰ ፡ እሱም ፡ የያሬድ ፡ ማኅሌት ፡ ነው ፡ የዳሞት ፡ ገዥም ፡ ካህናትን ፡ ያለፍርሃት ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የሕጉ ፡ ታቦት ፡ ፌት ፡ ቄመው ፡ ባያቸው ፡ ሠራዊትንም ፡ ላከ ፡ ከበቡዋቸውም ፡ ወደ ፡ እርሱም ፡ አመጡዋቸው ፡ ገዥውም ፡ የጠየቃቸው ፡ እናንተ ፡ ለምን ፡ አትፈሩም ፡ ከእኔስ ፡ አትሮጡም ፡ አላቸው።

፱ ፡ የእግዚአብሔር ፡ ካህናትም ፡ መለሱለት ፡ ከእጅህ ፡ የሚያድነን ፡ አምላካችን ፡ በሰማይ ፡ አለ ፡ ካንተ ፡ አንፈራም ፡ አሉት ፡ ንጉሡም ፡ አምላካችሁ ፡ ማን ፡ ነው ፡ ሲል ፡ ስለሳቸው ፡ ጠየቀ ፡ የጠየቃቸው ፡ እነዚያ የእግዚአብሔር ፡ ካህናትም ፡ የሰማይ ፡ አምላክ ፡ ያድነናል አሉት።

፲ ፡ ያ ፡ ገዥም ፡ መለሰ ፡ የድንኳን ፡ ካህናትንም ፡ ጠንቋዮች ፡ እንደሚሠሩ ፡ ኃይልን ፡ መሥራት ፡ ትችላላችሁን ፡ አላቸው ፡ አሁን ፡ ወደ ፡ እሳት ፡ ሳትቃጠሉ ፡ ትወጣላችሁን?

፲፩ ፡ እነሱም በአምላካችን ፡ በእግዚአብሔር ፡ ኃይል ፡ አም ፡ እንችላለን ፡ አሉት ነገር ፡ ግን ፡ እስከ ፡ ፵ ፡ ቀን ፡ ቀጠሮ ፡ ስጠን ፡ አሉት ፡ እንደጠየቁትም ፡ ሰጣቸው ፡ ከዚያ ፡ ጀምረውም ፡ በያሬድ ፡ ካህን ፡ የማኅሌቱን ፡ ዜማ ፡ በታላቅ ፡ ድምጽ ፡ የድንኳን ፡ ካህናት ፡ ወደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይፍጯኹ ፡ ጀመሩ ፡ መጠግያየ ፡ ኃይልየ ፡ የነፍስየ ፡ መድኃኒት ፡ ረዳቴ ፡ አንተንም ፡ ታመንሁ ፡ ኢ,ያሉ

፲፪ ፡ ይህችም ፡ ምዕራፍ ፡ አላት ፡ ገዥውም ፡ ለሁለተኛ ፡ የዳሞት ፡ ሰዎችና ፡ የጋፋት ፡ ሰዎች ፡ ለሁላቸው ፡ የባርያ ፡ ሰዎችም ፡ እስከ ፡ አርባ ፡ ቀን ፡ እንጨት ፡ ይሰበስቡ ፡ ዘንድ ፡ አዘዛቸው ፡ ሰበሰቡም ፡ ያ ፡ እንጨትም ፡ ኮረብታ ፡ (ተራራ) ፡ ያህል ፡ ክምር ፡ ሆነ ፡ በ፵ኛው ፡ ቀን ፡ መጨረሻም ፡ ገዥው ፡ ከጠንቋዮቹ ፡ ጋራ ፡ መጣ ፡ የድንኳኑ ፡ ካህናትም ፡ ከውሀ ፡ ጋራ ፡ መጡ ፡ ወሀ ፡ ይዘው ፡ ማለት ፡ ነው ፡ በያሬድ ፡ ካህን ፡ የማኅሌቱ ፡ ዜማዎች ፡ ጸለዩበት መኰንኑም ፡ እሳቱን ፡ ያነዱ ፡ ዘንድ ፡ አዘዘ ፡ ያን ፡ ጊዜ ፡ የእሳት ፡ ወላፈን ፡ ከፍ ፡ አለ ፡ ጠንቋዮቹም ፡ ሆዳቸውን ፡ የሚሸፍኑበት ፡ የላሞች ፡ ስብ ፡ እየለበሱ ፡ ገቡ ፡ ከእሳት ፡ መካከል ፡ በብረት ፡ ወንበራቸው ፡ ተቀመጡ።

፲፫ ፡ የድንኳኑ ፡ ካህናትም ፡ ፈጥነው ፡ ሮጡ ፡ ከእሳት ፡ መካከል ፡ ለነበሩ ፡ ጠንቋዮችም ፡ ከበቡዋቸው ፡ ያን ፡ ጊዜም ፡ በአብና ፡ በወልድ ፡ ስም ፡ በመንፈስ ፡ ቅዱስም ፡ ስም ፡ ሁለተኛም ፡ መጠግያየ ፡ ኃይሌ ፡ የነፍሴ ፡ መድኃኒት ፡ አንተንም ፡ ታመንሁ ፡ አሉ።

፲፬ ፡ እንደዚህም ፡ በያሬድ ፡ ካህን ፡ ዜማ ፡ ማየ ፡ ጸሎትን ፡ ረፈጹ ፡ በዚያን ፡ ጊዜም ፡ ሰይጣን ፡ የለበሱትን ፡ አስጣላቸው ፡ በእሳትም ፡ ተቃጠሉ ፡ አመድም ፡ ሆኑ ፡ አሠራቸውንም ፡ አልተገኘም ፡ በብረት ፡ ወንበር ፡ በእሳት ፡ መካከል ፡ የነበሩ ፡ የጠንቋዮች ፡ ቁጥርም ፡ ሦስት ፡ መቶ ፡ ሆነ።

፲፭ ፡ በያሬድ ፡ የማኅሌቱ ፡ ዜማ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያደረገው ፡ ተአምራትን ፡ እዩ ፡ ከአክሱም ፡ አጥብያ ፡ የድንኳን ፡ ካህናት ፡ የትምህርቱ ፡ ልጆች ፡ እጃቸው ፡ ጠንቋዮችን ፡ ፈጽመው ፡ አጠፏቸው ፡ አንድም ፡ አልቀረም ፡ ኢያሱ ፡ መስፍን ፡ በሕዝብ ፡ ፊት ፡ የኢያሪኮ ፡ ግንብን ፡ እንዳፈረሰ ፡ በካህናት ፡ ደወሎችም ፡ ኦሪት ፡ ሰዎች ፡ በታላቅና ፡ ጠንካራ ፡ ፊት ፡ ይጮሁ ፡ ደኑፉ ፡ እንዳለች ፡ የዙርያዋ ፡ ግድግዳም ፡ ወደቀ ፡ ወደ ፡ አገርም ፡ ገቡ ፡ ሁላቸውም ፡ በፊታቸው ፡ ሮጡ ፡ አገርም ፡ አገኙአት ፡ ኢያሱም ፡ ከሁላቸው ፡ የእስራኤል ፡ ሰልፈኞች ፡ ጋራ ፡ የኢያሪኮ ፡ ግንብን ፡ አፈረሳት ፡ መስፍን ፡ ነውና ፡ እነዚህ ፡ ካህናትም ፡ የሰይጣን ፡ (የጣዖት) ፡ ግንብ ፡ አፈረሱ ፡ ጠንቋዮችም ፡ ገደሉ ፡ አረማውያንንም ፡ ከአለቆቻቸው ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ እምነት ፡ መለሱ ፡ ንጉሥና ፡ አለቃ ፡ ጠሮኞችም ፡ ሳይኖራቸው ፡ እሳቸው ፡ ግን ፡ የያሬድ ፡ ካህን ፡ የማኅሌቱ ፡ ፊት ፡ የጦር ፡ መሣርያን ፡ አደረጉ ፡ ታግለውም ፡ ሰይጣን ፡ አሸነፉት ፡ ለአለቃም ፡ ጠንቀቂዮችን ፡ ይገድሏቸው ፡ ዘንደ ፡ አደረጉት።

፲፮ ፡ ስለዚህ ፡ ያሬድ ፡ ካህን ፡ ተጋደለ ፡ አሸነፈም ፡ የትምህርቱ ፡ ልጆች ፡ ካህናትንም ፡ በማኅሌተ ፡ ዜማ ፡ አጋደለ ፡ በጣፋጭ ፡ የማኅሌቱ ፡ ዜማ ፡ በምድረ ፡ ዳሞት ፡ ብዙ ፡ ቀን ፡ ተቀመጡ ፡ የሚረዳቸው ፡ ንጉሥ ፡ የሚያረጋጋቸው ፡ መልአክም ፡ ሳይኖራቸው ፡ ረዳትና ፡ አረጋጊ ፡ የያሬድ ፡ ካህን ፡ የማኅሌቱ ፡ ፍጬሽት ፡ ሆናቸው ፡ እንጂ።

፲፯ ፡ ከብዙ ፡ ዓመታት ፡ በኋላም ፡ እግዚአብሔር ፡ የሚረዳቸውና ፡ የሚያረጋጋቸው ፡ ከዳዊት ፡ ቤት ፡ ከይሁዳ ፡ ወገን ፡ የተገኙ ፡ የአንበሳ ፡ ልጅ ፡ ንጉሥ ፡ የይኩኖ ፡ አምላክ ፡ የልጅ ፡ ልጅ ፡ ዓምደ ፡ ጽዮንን ፡ ላከላቸው ፡ የዓምደ ፡ ጽዮንን ፡ በሃይማኖቱ ፡ የቀና ፡ እና ፡ እግዚአብሔርን ፡ የሚወድ ፡ ነው ፡ ያለ ፡ እግዚአብሔርም ፡ ሌላ ፡ አምላክ ፡ አያውቅም።

፲፰ ፡ ወደ ፡ ምድረ ፡ ዳሞትም ፡ ሄደ ፡ ከሱ ፡ ደርሶም ፡ ሁላቸው ፡ ዓላውያን ፡ ቀጠቀጣቸው ፡ በአምላኩ ፡ በእግዚአብሔር ፡ ኃይልም ፡ ሥልጣናቸውን ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ መለሰላቸው ፡ ወደፊተኛው ፡ ሥራታቸው ፡ ሠራቸው ፡ ሕዝበ ፡ ክርስቲያንም ፡ ዛጌ ፡ በሚባሉ ፡ የአሕዛብ ፡ መንግሥትነትና ፡ እንዳልወደደ ፡ አዩ ፡ ድሮም ፡ (ፊትም)፡ የእስራኤል ፡ መንግሥትና ፡ የምራራ ፡ ሥልጣን ፡ አንጀቱን ፡ ወጥቶ ፡ በክፉ ፡ ሞት ፡ ሞተ።

፲፱ ፡ ለዜና ፡ ጴጥሮስም ፡ የዳሞት ፡ ምድር ፡ ዓረማውያን ፡ ራሱን ፡ ቈረጡት ፡ ለራሱም ፡ የእህል ፡ መሥፈርያን ፡ አደረጉት ፡ ለሱም ፡ የዜና ፡ ጴጥሮስ ፡ ራስ ፡ አሉ ፡ ሰንት ፡ ፈትም ፡ አወጣ ፡ እግዚአብሔር ፡ ያደረገውን ፡ እዩ ፡ ከቅድስት ፡ ድንግል ፡ ለተወለደ ፡ እግዚአብሔር ፡ ቃል ፡ ለሚያመልኩት ፡ እስራኤል ፡ የሰጣቸው ፡ መንግሥትነትን ፡ ከፈቀደ ፡ ዘንድ ፡ በአሕዛብ ፡ እጅ ፡ ይቀማ ፡ ዘንድ ፡ አይቻልም ፡ በሁሉ ፡ ዘመንም ፡ ምሕረትና ፡ ሣህል ፡ ከእሳቸው ፡ አይርቅም ፡ የሚያውቋቸውም ፡ ለጥፋትና ፡ ለሙስና ፡ ናቸው።

፳፪ ፡ በሥሉስ ፡ ቅዱስ ፡ እምነት ፡ በወንጌል ፡ ሃይማኖት ፡ የኢትዮጵያ ፡ ነገሥታት ፡ መንግሥትነትን ፡ ለሚጠብቅ ፡ እግዚአብሔር ፡ ምስጋና ፡ ይገባዋል ፡ የጠና ፡ መንግሥታቸው ፡ ወንበርንም ፡ የማያነዋውጥ ፡ ስለዚህ ፡ እንደሚያበራና ፡ እንደሚያሸበርቅ ፡ ፀሐይ ፡ በኃይል ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ ይላልና ፡ ይሄዳል ፡ የቅዱስ ፡ ያሬድ ፡ በረከት ፡ ከአገልጋዮቹ ፡ ከ ና ፡ ከ ጋር ፡ ይኑር ፡ ለዘለዓለሙ ፡ አሜን።